ውግደ ዲያብሎስ ወራጅ አለ

In memory to all Ethiopians who sacrifice their life for justice and democracy in the true meaning of the slogan

Paul demands active unity in the church, “ A unity that explicitly joins together differing ethinc groups because of their common identity in Christ. …… The old barrier form of brand-new humanity.The old barrier of hostility has been demolished by the cross, and now, all peoples are to be one in christ” Rom,4. Gal 3-4; col 3

ቅዱስ ጳውሎሰ በቤተ ዕምነት አንድንትን ሰብካል እንዲህም አለ “ሁሉንም ብሄር፤ ቀለም፤ ዘር የሚያጣምር አንድነት ወሳኝ ነው ምክንያቱም ሁሉም በክረሰቶሰ ፊት አንድ ነው፡፡፡፡ የነበረው ኩራትና ትዕቢይት ከላይ ላያቹህ አንሰቶቷል፤፤ ሁላችሁም የአዳም ዘር ናቹሁ፤፤ አዳምም የተፈጠረው ከአፈር (ከጭቃ) ነው፤፤ በርግጥ ጥሩ አገልጋይ የአላሃ ዕወቀት ያለው ነው፤፤”

“No one is born hating another person becauseof the color of his skin, or his background, or his religion. People must learn to hate, and if they can learn to hate, they can be taught to love, for love comes more nautrally to the human heart than its opposite.” Nelson Mandela

“ማንም ቢሆን ሰውን በዘሩ፡ በሃይማኖቱ፡ በቀለሙ ለመጥለት አለተወለደም፡፡ ጠላቻን ይማረዋል እንጂ፡፡ ለመጥላት ማሰተማር ከተቻለ፡ ለመወደደና ለማፍቀር ማሰተማር ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ፍቅር ከጥላቻ በበለጠ ተፈጥራዊ ነውና፡፡ ኒልሴን ማንዴላ

ዑነቱ ይህው ሲሆን ጥላቻን ትዕቢትን በምላሱ በአእምሮው ይዞ የሚወለደ ወይም የተወለደ የለም፡፡ ችግሩ ሰዎች ከቁሱ ዓለም ሲገናኙ በሚያገኙት አዲስ ስነ ልቦናና  አፍቅሮተ ንዋይ የቁሳዊ ዓለም እስረኛነት  ግለኝነት ያዳብራሉ የሚያመነጨሉ፤፤ “ ያመቻል የሚሉት ብልሃት ይቀይሳሉ፤፤ ስለሆነም ሰዎች ለዚህ ዓላማቸው ይርዳቸው ዘንድ የራሰቸውነ ዘር ለማጎልበት ተጨባጭነት የሌለው በምናባቸው ብቻ የቀመሙት የበላይነት በቀለም፤ በዘር፤ በጎሳና፤ በጎጥ ማቀነቀን ይጀምራሉ ይህም ከትውለድ ወደ ትውልድ ይመነዘራል፤፤

በየዘመኑ የሚከሰቱ ሁኔታዎች በሚያመቻቸው እየተረጉሙ ዜማውና ቅኝቱ እየተቀያየረ የአንዱን የበላይነት ሲያጎሉ የሌላውን የበታችነት ይሰበካሉ፤፤ እንደ ዑነቱ ከሆነ ግን በስሙ የሚወራለት አብዛኛው የሕብረተ ሰብ አባል የሚተረፈው ስምና አላሰፈላጊ መስዋዕትነት መከፈል ነው፤፤ ባለፉት 27 ዓመታትም ሆነ ከዚያ በፊት በሃገራችን ያየነው ዑነታም ይህ ነው፤፤ በየጊዜው በሀገራችን በረከት ያሉ ለወጥ ፈላጊዎች እንደ ገንዛቤያቸውና ወቅቱ በሚፈቅደው ታግለዋል መስዋዕትም ከፍለዋል፤፤ይሁን እንጂ በተከፈለው መስዋዕት ሽፋን ተጠቃሚ የሆኑ አፈ ጮማዎች(ጮሌዎች) በተሰውት እይማሉና እየተገዘቱ የዓዞ ዕንባ እያነቡ ፈሩ እንዲለቅ አድርግውታል፡፡ቡዙዎች አምነውበትም ሆነ በጊዜ አሰገዳጅነት ወደ ትግሉ ዓለም የተቀላቀሉ ውድ ሕይወታቸው ቢከፍሉም የታገሉለት ዓላማ መዝረክረኩ ቀና ብለው ቢያዩት የደም ዕንባ ያለቅሱ ነበር፤፤

በዚህ ሁሉ ጊዜ በአንድነት ዙርያ የሚያቀነቅኑ እንጂ በጎጥ፤ በጎሳ የሚያነበንቡ አለነበሩም፤፤ በርግጥ በ1960ዎቹ መጀመርያ ጥቂት የአዲስ አበባ ዩኒበርሰቲ ተማሪዎች የብሄር ጥያቄ አቀነቅነዋል ቡዙም ባይገፉበትም፤፤ ይሁንና በተለያየ ጊዜ ብልጭ ድረግም ቢልም አፍጦና እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ከልክለው በሚል ፈሊጥ መተግበር የተጀመረው ከ1983 ወዲህ ሲሆን የተዛባ ትርጉም እየተሰጠውም ለዘመናት በአበሮነት በኖረው ሕዝብ መካከል የመጠራጠር በጎሪጥ የመተያየተና ሲበሰም የሕይወት ዋጋ አሰከፈለ እያሰከፈለም ነው፤፤

እዚህ ላይ ጥላቻን በሚሰበኩ ፍቅርን በሚያንካሰሱ በሚነዙት ሰብከት አዙሪቱ እየናረ አብሮነትን ፍቅርን ሊንደው እየታገለ ነው፤፤ ይህን የጥላቻ ነጎድጋድ ማንንም የሚጠቅም ባይሆንም ጥቂቶች የገበያ ግርግረ ለሌባ ይመቻል እንዲሉ አጋጣሚውን ለግል መጠቀምያና ደህነት ማራገፍያ ሊያደርጉት ሲራራጡ፡ሌሎችም ዘረፋንና የማይገባ ጥቅማጥቅ ለማካበት እንደ ስለት ሊጠቀሙበት ዳርዳር ሲሉ ይታያሉ፤፤

እንደ ዑነቱ ከሆነ ጊየዜውን ጠብቆ ለውጥ እያነዣበበ ነው ቁምነገሩ ይህን ለወጥ የሚሸከም አእምሮና ማሰተዋል እየተናነቀን ነው፤፤ ጥያቄው ለውጥስ መጣ እኛስ ለለውጡ ተዘጋጀተናል የሚለው በግለጽና በማያሻ መንግድ ተግባራዊ ምላሽ ያስፈልጋዋል ነው፤፤

ታዋቂው ፖለቲከኛና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የታላቅዋ ብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒሰተር የነበሩት ዊኒሰተን ቸርችል "To each there comes in their life time a special moment when they are figuratively tapped on shoulder and offered the chance to very special thing, unique to them to fitted to their talents.What a tragedy if that moment finds them unprepared or unqualified for that which could have been their finest hour." " በሕይወታችን ዘመን በአንዱ ወቅት ምሰሌያዊ የሆነ ተግባር እነድንከውን ጥሪ ሊየደርሰን ይችላል፤ ለየት ያለና አቅማችን የሚመጥን፤፤ ሆኖም ግን ይህን ዕድል ባለመዘጋጀታችን አልያም በብቃት ማነሰ ወርቃማው ዕድል ከእጃችን ሲያመልጥ እጅግ አሳዛኙ ነገር ይህው ነው፤፤"

ዛሬ ያለንበት ጉዳይም ይህን ሁኔታ ያንጸባርቃል፤፤ ሁላችንም የማህበራዊ ሚድያ እሰረኞች ሁነን በምናቀውም በማናቀው እንደ ቦይ ወኃ በተቀደደለን ፈለግ እየተጋዝ ነው፤፤ ይህም በአንድ ብሄረሰብ የተወሰነ፤ በዕድሜ፤ በትምህርት ደረጃችን ሳይሆን ድፍን በሆነ ሰሜታዊነት ጉዞ ላይ ነን።

ይህ አካሄድም ለማንም ለምንም ጠቀሜታ የለውም፤፤ ዊኒሰተን ቸርችል እንዳሉት ወረቃማው ዕድል ለማሰተናገድ ዝግጅት አልባና ብቃት አለባ ሁነን ዓይናችን እያየ ዕድሉ ቢያመለጠን የመንሞተው ያኔ ነው፤፤

በማነኛውም የሕይውት ዕንቅንስቃሴ ብቃትና እውቀት በተራ አሉባልታ ዋጋ ሲያጡ በወሬ ዋጋየለሹና ብቃት አልባዎች ይገናሉ፤፤ ጥሩ አናፋሽ ያላቸው ሲሞጎሱ አብረን እናወድሳለን፤ ብቃቱም ዕውቀቱም ያላቸው በየመድረኩ ብቅ ጥለቅ ሰለማይሉ ሲወገዙ አበርን እናወግዛለን፤፤ አውቀዋሎህ ብለህ ከምትወራረድለት ሰው ውስጥ ሌላ ፍፁም የምታውቀው ሰው አለ የሚለው የአበው አባባል ወደ ጎን ትተን ድርጊታችንም በተጨባጭ መረጃና በዕውቀት ሳይመሰረት ንፋስ እንደሚወዛውዘው ዛፍ ግራ ቀኝ ስንወዛወዝ ወረቃማውን ዕድል እያመለጠን ነው፤፤

ዘረኝነት እያወገዝን ራሳችን በሌላ መልኩ እኛው እናራግበው አለን፤፤ በሌላው ያወገዝነው በቃላት ከሸነን ቀለም ቀባበተን ብናራመደው አልሸሹም ዘወር አሉ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፤፤ የዚህ ኩብር ሕዝብ የአብሮነት ታሪክ አከብረንና አድመጠን መዳዝ ግድ ይላል፤፤

አሁን ምረጫችን አንድና አንድ ነው፤፤ ዘመኑም የሚጠይቀው ይህ ብቻ ነው፤ ዓለም በጉለባላይዘሽን ሽርጉድ በምትልበት እኛ በጎጥና በመንደር መላተማችን ችረችል እንዳሉት የሞት ሞት ነው፤፤ ፊተ ለፊታችን ያለው ዑነት መቀበል የግድ ይለናል። ይህን ዳባ ልበስ ማለት ዋጋ ያስከፍለናል፤፤ ዕድሜያችን አጋምሰን ወደማይቀረው ዓለም ጉዞ የጀመርነውም ለቀሪው ትውልድ ዘመን የማይሽረው ጠባሳ ላለመተውና ነገን ሊጠቅም በሚችል ጉደይ አተኩረን በምክረና በዕውቀተና የልምድ ሽግግር ላይ ብናተኩር፤ ትወልድ/የዕድሜ ከፍተቱ በማጤን ጭምር፤፤ ሙሁራንም ቅን በሆነ መልኩ ለትውልድ የሚሆን በአንድነት በፍቅር ዙርያ ዑነትና ዑነት ብቻ ተሞርኩዞ ትውልድን ማነጽ ይጠበቅበናል፤፤ ይህም የውዴታ ግዴታችን መሆኑ ብንረዳ። የኔ ብሄር አልተሾመም የኔ ይህን አላገኝም ሳይሆን ቅድሚያ ለኢትዬጵያዊነትና ለብቃት ብንስጥ በአንድነት ለመኖር የማዕዝን ዲንጋይ ይሆነናል።

በታሪከ አጋጣሚ ሥልጣን ላይ የነበራቹሁም እንደ ሰደደ እሳት ሳይታሰብ የተቀጣጠለው ለውጥ ከእልህና ከተደፈርኩ አባዜ ወጥታቹህ ለውጡን መልክ ማስያዝ አልያም እኛ እዚህ አደርሰናል ቀጣዩ ትውልድ ደግሞ ያስቀጥለው በሚል ቀና አሰተሳሰብ ድጋፍ መሰጠት ይጠበቅባቹኃል ከዚህ ውጭ የሚደረግ እንቅስቃሴ ያለፈውን ስራቹህ ጥላሸት ከማልበሱ በላይና ሕዝብን ከሕዝብ በማባላት አላሰፈገላጊ ዋጋ ሊያሰከፈላቹህ ይችላል፤፤ በርግጥ የሕዝቦች የአብሮነት ታሪክ ለሚያቅና ነባራዊ ሁኔታው እንደሚሳይው ኢተዮጵያ ውሰጥ ሰሜታዊ በሆነ ምክንያትና በአንዳንድ ግልብ የፖለቲካ ነጋዴዎች ቅስቀሳ እዚህም እዛም ጉዳቶች መድረሳችው አይቀርም ደርሳልም፤ ሕዝብን አትናቁ ሕዝብ ብዙ ነገር ያውቃል የየትኛውም ብሄር ሕዝብ ዝምታውን እንደአልዋቂና እንደ ሽንፈት አትቁጠሩት። ትዕግስቱ አብቅቶ በቃ ያለ ዕለት እንደ ደራሽ ወንዝ ነውና።

ማንም ይሁን ማንም በመካከለኛ ምሰራቅ፣በአፍጋኒሰታ፤ በኢራቅ፡ በሶርያ፡ በየመን፤ በሶማሊያና በደቡብ ሱዳን የሆነውና እየሆነ ያለው ለህሊና የሚሰቀጥጥ የቤተሰብ መበተን፤ አንደወጡ መቅረትና በህዝብ ላይ እየደረሰ ያለ ኢስብዓዊ ሁኔታና ዘግናኝ ትዕይንት የተመለከተና የተከታተለ፤፤ መሰል ትይንት በሀገሩ ማየት የሚፈልግ ካለ ጤነኛ ነው አልልም፤፤ እሰኪ በማያቀውና ምንም በቀውሱ አሰተዋጽኦ ሊኖረው የማይችል ግን በቱርክ የባህር ዳርቻ በደረቱ ተደፍቶ ዓለም ያየው የሶርያው ህጻን የኔ ልጅ ቢሆን፤ የልጄ ልጅ ቢሆን ብለን በዓየነ ኅሊናችን እናስብ፤፤ መልሱን በየግላችን እናሰላስለው፤፤

ምንም እንካ የአገራችን የታሪክ ጸሀፊዎች ዓፄ ቴዎድረስን በጭካኔያቸው ብዙ ጊዜ ቢያነሰዋቸውመ የውጭ ጸሃፊዎች አረቆ አሰቢነታቸውን እሳቸው ካለፉም ቢሆን በሚያደረጉት ድርጊት ሕዘባችውና ሀገራቸው ጉዳት እንዳይደረሰበት ይቆረቆሩ እንደነበር መሰከረወላቸዋል፤፤ እነግሊዞቸ መቅደላን ለመውረር

በዘመቱበት ሰአት ታማኝ ጦር አዛዦቻቸው ገበርዬ ከሞተ በኃላ ሞካንንቶቻቸው በጃችን ያሉ የእንግሊዝ እስሮኞች እንረሸናቸው ብሉ " ይሀማ አይሆንም ይህን አደርጌ ለሀገሬና ለሕዝቤ ዕዳ አለተውም" በማለት ድርጊይቱ እንዳይፈጸም በመከልከል ውድ ሕይወታቸውን በጀግንነት ራሳቸውን ሰውተዋል፤፤ የእሰረኞቹ መረሸን እንግሊዞች ሊወሰዱት ይችሉ የነበረ የበቀል ዕርምጃ አስቀድመው በማስብ አከሸፈውታል፤፤ በዚህም መሪ ከሕዝብና ከሀገር በላይ እንዳልሆነ አስመስከረው አልፈዋል፤፤

ኩሩ ሃገር ወዳዶች እንዲህ ያደረጋሉ፤፤ ከራሳቸው በላይ ሕዘብን ሀገረን ያስቀድመሉ፤፤ ዓጼ ዮሀንስ በጉበኝት የመጡ ነጮች ሲሰኑ አሽከራቸውን ምጽዋ ሲደርሱ ጫማቸውን አውጥተህ እጠበው የሀገሬን እፍኝ አፈር ይዘው እንዲሄዱ አለፈለግም ነበር ያሉት፤፤ ከኮለኔል አብዲሳ ጋር በእሰር የነበረ አንድ ጸረ ፋሺሽት የጣልያን ተወላጅ ባሰፈረው ማሰታወሻ "አብዲሳ ልዩ ሰው ነው፤ ሁሌ የማይለየው የሀገሩ ባንዴራ እያየ ሀገሬ ሕዘቤ ናፈቀኝ አየሩ አፈሩ ይሸተኛል" ይል ነበር፤፤ በመጀመርያ አብረነው የነበርን ብዙም ተኩረት አለሰጠነውም ከእሰር ካመለጥን በኃላ ግን እኛም አባባሉ ውሰጣችን በመሰረጹ እንደ የራሳችን ጀግና እንመለከተው ጀመር፤፤ ሲል በጣሊያንኛ ቋንቋ ባሰፈረው የግል ማሰታወሻ አሰነብባል፤፤

ኢትዮጵያ በነዚህና ቁጥር ሰፈር በሌላቸው ጀግኖች በፍቅር፤ በአብሮነት፤ ከብሄር፤ ከአከባቢ፤ ከጎጥ ውጭ በአንድ ባንዴራና ዓላማ ተዋድቀው ስላቆያውት ነው፤ ዛሬ ኢትዮጵያ በቀኝ አገዛዝ ወድቃ አታውቅመ እያልን የምንፎልለው፤፤ በውድ ሕይወታቸው፤ በደማቸውና በአጥንታቸው የገነቡት መሰረት መናድ ባይቻልም ሙከራው እነዳለ የአደባባይ ሚስጥር ነው፤፤ በተለይ በአንዱ የሀገራችን አካባቢ አንዳንድ በሃይማኖት ሰበብ የገቡና በጦርነት ያለተሳካ የቅኝ ግዛት ህልም በኃይማኖት ለማሳካት የሞከሩትና ጥቂት የሚባሉ ሰዎች ማሰባሰብ የቻሉ ድበቅ ዓላማቸው እንኳ መሉ በሙሉ ባይሳካም የጣሉት የመርዝ ሰነኮፋ ሙሉ በሙሉ ባለመነቀሉ በየጊዜው እንደ ችገር በቅ ጥልቅ ማለቱ አልቀረም፤፤

ይሁንና ኢትዮጵያውነት የቀለም ቅብ ሳይሆን በደምና በዘረ መል የሚተላለፍ መሆኑ ምልክቶች እያየን ነው፤፤ በቅርቡ በዶ/ር ዓብይ የጀርመን ጉብኝት ያየነው ለዚህ ግልጽ ምስክር ነው፤፤ የኦነግ አርማ ይዘው (መያዛቸው መብታቸው እንዳለ ሆኖ) በስበሰባው የተገኙ የኦሮሞ ብሄር አባላት በተለያየ ቋንቋ  በቀረበው የሙዚቃ ዝግጅት በአብሮነት ሲሳተፉ ማየት፡ የኦረቶዶክስ፤ የእስለምና ሀይማኖት ተከታይዎች በቢሄራዊ ሰንደቃላማ አጊጠው በጋራ ማየት የሚደነቅና ተስፋ ጫሪ ነው፤፤

በዚሁ መድርከ ኢትዮጵያወያን ሙሰሉሞች ዓለምን ያስደመመ ተግባርም አሰይተዋል፤፤ በቢሄራዊ ሰንደቃቸው ተውበው ከበሄር ከዘር ባሻገር በጋራ ቆመው መታየታቸው ልበ ላል  ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለመላ ዓለም ትልቅ መልዕከት አሰተላለፈዋል፤ የቅዱሰ ቁራን ትመህረትንም ተገባራዊ አድረገዋል፤፤

"O' Humanity! Without doubt we have created you from a male and a female and have made you into various nations and tribes, so that you may come to know and understand one another. Definetely the most hounoured among you in the sight of Allah is the one who is the most Allah Consciouness. Surely Allah has full knowledge and is All-Aware."

"ሠዎች ሆይ! ያላንዳች ጥርጥር የተፈጠራቹሁት ከወንድና ሴት ነው፤፤ ከዛም በተለያዩ ብሄርና ጎሳ ተከፋፈላቹህ ምክንያቱም እነድትተዋወቁና አንድትግባቡ ነው፤፤ በርግጥ ከማሃከላቹህ ከብረና ሞገሰ የሚያገኘው አላህን የሚያውቅና ትዕዛዙን የሚፈጽም ነው፤፤ አላሀ ስለ ሁሉም ነገር ያውቃልና፤፤"  አስተምህሮ ተግባራዊ በማደርግ የኢትዮጳወያን በሳል አእምሮ አሳይተዋል፤፤

ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን የእስልምና ዕምነት ተከታዮች ምንም እንኳ ብሶትና ችግር የላቸውም ባይባልም አሁን ሀገሪቱ ባለችበት ሁኔታ የኛ ችግር አይብስም በማለት እያሳዩት ያለ ምግባር ማድነቅና ማመስገን ተገቢ ነው። ከግል ችግር የሀገር ጉዳይ በማአስቀደምቸው። ሁሉም የእምነት ተከታዬች ተባረኩ ኮራንባቹህ ቢባሉ ያንስባቸዋል እንጂ አይበዛባቸውም።

እትዮጰያና ኢትዮጵያውያን ዛሬ የሚያስፈልገን ፍተህን፤ዕኩልንተን፤ማረጋገጥ ከሁሉ በላይ ድህነትን መፋለመን ነው፤፤ ሁላችንም የዚች ሀገር የ ቦኩር ልጆች እነጂ የእንጀራ ልጂና የቦኩር ልጅ የምንባባል አይደለንም፤፤ ታሪካችንም የሚያሳየው ሆነ በተጨባጭ መሬት ያለው ዕውነታ የትም እነሰፈር የትም በአብሮነት በፍቅር ኖረናል እየኖረንም ነው፤፤ አሁን የተፈጠረው ይህ የኔ ነው እኔ እገሌ ነኝ አነተ እነትና ነህ የብዛሁኑ ኢትዮጳያውያን ስሜትና ፍላጎት አይገልጽም፤፤

ለዘመናት በብሄረ በጎሳ ራሱን ሳይመነዝር በኢተዮጲየውነቱ አበሮ የኖረ የሚኖር ሕዝበ ጥያቄም አይደለም፤፤ አያ ጂቦ ሳታማሐኝ ብላኝ ካለሆነ በስተቀር፤፤ ኦሮሞው ማነህ ማነሽ ሳይል የቡናና የእረሻ መሬየቱን እያካፈለ ዘር ጎሳ ሳይመረጥ፤ ማደጎ እነኳ ወሰዶ ሲያሳድግ የጎሳ የዘር ጥያቄ አንስቶ አያውቅም፣ አማራውም፤ ትግሬውም ሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችም እንዲሁ፤፤ የትም ይሁን የትም አበሮ በፍቅረና በአበሮነት በመኖሩ አሁን ያለው ትወልድ ዘር ቁጠር ቢባል ቀላል የሂሳበ ሲሌት አይሆንለትም፤፤

ለጊዛያዊ ፖለቲካ ጥቅም ተብላ በማር ተሸፍና የቀረበችልን ድገሰ ወዲያ ብለን የኦረቶዶከስ ተከታዮች ዓርብ ስቀለት ሌሊት የክረሰቶሰን ትንሳኤ ለማብሰር “ ኮነ ፍስሀ ወሰላም አሰሮ ለሰይጣን አግአዘ ለአዳም” እንደሚሉት እኛም “ ኮነ ፍስሀ ወሰላም አሰሮ ለዘረኝነት፤ ለፈተህ አልባነት፤ ለትዕቢት አግአዞ ለአንድነት፤ለአበሮነት፤ ለዕኩልነት” እያልን የኢትዮጵያን ትነሣኤ ብናበስር ለሁላችንም ይበጀናል፤፤ ልባችን በአፍቅሮተ ንዋይ፤ በጥላቻ፤ በሥልጣን የታወርንም ይህችን የአባቶች ምከር በናጤናት “መሬት(ኢትዬጵያ) አትቆጬ ቀስ ብዬ እረገጣሎህ ነገ ካነቺ በታች ሞሆኔን አወቃሎህ” ነገን እናሰተውል.፤፤ ተሰፋን መልካምን የሚመኙ ሁሌ በችግረ ወሰጥ መልካም ዕድለን ያያሉ፤ ተሰፋ ቢሶች መልካም ዕድል ባለበት ሁኔታ እንኳ ችግር ይታያችዋል እኔ ከሞቱኩ ....... ናቸወና፤

በዚህ የዘር፤ የኃይማኖት በፖለቲካ ወገንነት አባዜ ለሚዳከሩ Dr. Chuba Okadigbo የተባሉ የናይጀርያ የፖለቲካ ሙሁር እንዲህ  ይላሉ “ If you are emotionally attached to your tribe, religion or political leaning to the point truth and justice become secondary considerations, your education is useless, your exposure is useless. If you can not reason beyound petty sentiments, you are a liability to mankind “

“በስሜታዊነት፤ ከጎሳህ፤ ከኃይማኖትና ከፖለቲካ። ወገንተኝነት ራስህን አቆራኝተህ ዑነትና ፍትህን በሁለተኛ ደረጃ ከፈረጅክ፤ መማርህና መውጣትህ ጥቅም የለውም። ከስሜታዊነት ምክንያታዊ መሆን ካልቻልክ ያንተ መኖር ለስብዓዊ ፍጡር ህልውና መስናክል ነህ።”  ሲሉ አስፍረውታል። ልቦና ይስጠን።